# መቀነስ የት ገባ?

ኢትዮጵያዊነትን ፣ ልናሳይ በተግባር
አይነኬን ጭምር ፣ ልናደርገው አባር
ገና ዳዴ ስንል ፣ መደመር ስንማር
መቼም ለአህዮ ፣ አይጥምምና ማር
መቀነስ ጀመረ ፣ የቀን ጅብ በምግባር ።

ሂሳብ አይገባቸው ፣ ማባዛት ፣ ማካፈል
መደመር ቢሆን ፣ መጨመር ፣ መታከል
እኔ ብቻ የሚል ፣ ተጣብቶት ክፉ አመል
ክምር ሲንድ ያድራል ፣ የቅነሳው አምበል ።

መማር ከተባለ ፣ እንማር በቅጡ
አራቱም መደቦች ፣ ባግባብ ይቀመጡ
የሂሳቡን ህጎች ፣ ስርዐት አትለውጡ
አባዝቶ ፣ ማካፈል ፣ ደምሮ ፣ መቀነስ
… ለሂሳብ ነው ጌጡ ።

ማባዛት ማካፈል ፣ የማያውቅ ተማሪ
መቀነሱ ይበልጥ ፣ ከሆነ አስቸጋሪ
ያገኘውን ሁሉ ፣ ከሆነ ደማሪ
አሰሱን ገሰሱን ፣ ይሆናል ከማሪ
መቀነስን የሚያውቅ ፣ ይሻል አስተማሪ ።

ማባዛት ፣ ማካፈል ፣ ካልተማርን እሱን
ባንድ ስሌት ብቻ ፣ ከምንሆን ውሱን
ተምረን እንወቅ ፣ እኛም መቀነሱን
ሁሉም በያለበት ፣ ይፈትን እራሱን
ደምረን ቀንሰን ፣ እናግኘው መልሱን ።

ስሌቱ አይሰራም ፣ ኔጌቲቭ ደምሮ
መቀነስ ይሆናል ፣ ድምር ፣ ዞሮ ዞሮ
አይሰራም ሂሳቡ ፣ የኔጌቲቭ ድምር
ከስጋ አይቀይጡም ፣ የልፋጩን ክምር
ከጤነኛው አፕል ፣ ብልሹ አትደምሩ
የበሰበሰውን ፣ መቀነስ ተማሩ ።

እንዴት ነው ሂሳቡ ፣ ስሌቱ ተዛባ
ከመደመር በቀር ፣ ማባዛት ፣ ማካፈል
… መቀነስ የት ገባ?

ታዛቢው

June 28, 2018